ሰኔ 21ቀን 2013 ዓ.ም

# የዐማራን ህዝብ ማጥፋት ለምን አስፈለገ?

የኢትዮጵያ አፍራሽ የሆኑት መለስ ዜናዊ ግበረ አብሮቹ በኢትዮጵያውነቱ በማይደራደረው አማራ መቃብር ላይ የቀንቅዠታቸውን ታላቋን ትግራይን ለመመስረት በ1968 ደደቢት በርሃ ገቡ። በአወጡት ማን ፌስቶ አጠቃላይ የአማራ ሕዝብ በኢኮኖሚው ተጠቃሚ ሲሆን ሰፊዉ የትግራይ ህዝብ ግን ሥራ አጥቶ-- በስደት፣በርኃብ፣ በድንቁርና፣በበሽታ ወዘተእየተሠቃየ እንዲኖር አድርጎታል።ከአማራ ሕዝብ ጭቆና ነጻ የሆነ የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ እንመሰርታለንበሚል ሁነኛ ጸረ አማራ ዓለማ ነበር መነሻቸው። ለዚህም 27 ዓመት ሙሉ በአማራው ሕዝብ ላይ የፋጸሙት የዘርማጥፋት ተግባር ታሪክ የማይረሳው ለትውልድ የሚተላለፍ ሕያው ምስክር ሆኖ ይኖራል። የዚህ ጽሁፍ መነሻ አንኳር የነመለስና ተባባሪዎቻቸው የአማራ ጥላቻ መነሻ ነጥቡን በመጠኑም ቢሆን ለመጠቆም ነው። ህወሃትና ገረ አበሮቻቸዉ ይህን ያህል የእውነት ጭብጥ የሌለው ጭፍን የአማራ ሕዝብ ጥላቻ ለምን አደረባቸው? ሕዝብስ እንደ ሕዝብ በሙሉ ከምድረ ገጽ እስኪ ጠፋ ድረስ ይጠላል ወይ?

አጼ ዮሀንስ ከሞቱ በኋላ በዳግማዊ ምኒልክ አማካይነት ትግራይ በሽዋ ማእከላዊ ግዛት ሥር ወደቀች። ከዚህ በኋላ በዐማራዉ መሳፍንት ቡድን እና ተከታይዎቹ የትግራይን ነጻነት ገፈዉ የህዝቧን አንድነት አናጉት፡፡ የትግራይ ህዝብ በድንቁርና፣ በበሽታ፣ በርሀብ፣ አዘቅት ዉስጥ እንዲሰምጥ አደረጉት፡፡በግድ ዐማራ ለማድረግ የአልሞከሩት ዘዴ ባይኖርም መሬቷ ተቆራርሶ የተወሰደባት ህዝብ የሚኖርባት ጭቁን ብሄር ሆነች የሚል ትርክት ይዘው የነ መለስ ቡድን ተነሳ።አላማውም ከአማራ ሕዝብ ብሄራዊ ጭቆና ነፃ የሆነ የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ማቋቋም በሚል ነው።ከጅምሩ ይህ የትህነግ አካሄድ ትክክል አለመሆኑን የሚያመከልተውና የመሬት ወረራና ቅርምት መሆኑን የሚያሳየው ትልቁ ማስረጃ የትግሬ ዳር ድንበር የሆነውን የተከዜ ወንዝን ተሻግረው መምጣታቸዉ ነው። ከመሬት ወረራው በተጨማሪ ትህነጎችና አሸከሮቻቸው ለአማራው ሕዝብ ያላቸውን ስር የሰደደ ጥላቻ በሚከተሉት ንግግሮቻቸው ሲገልጹ ኑረዋል።

፩-- ስብሃት ነጋ አማራ እና የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን አንኮታኩተነዋል። ገድለን ቀብረነዋል።

፪--መለስ ዜናዊ መሬት የህዝብ እንዲሆን አለቃዉ ኸርማንኮ ሲጠይቀዉ አይሆንም ምክንያቱም ዐማራ መሬት እየገዛ ሌላዉን ያደኸያል ፡፡

*.በአማራ ላይ ያዘመትነዉ አማራ ነን ያሉትም ሌሎችም በአማራ ላይ የዘመተ ነዉ ስንል የአለፉት የቅርብ እና የሩቅ ጊዜ አጼዎቻችን በሰጡን ኢትዮጵያ ላይ ነዉ፡፡ምሳሌ አንድ ሰዉ መንገድ ለማዉጣት ደን የሚመነጥረዉ ከደኑ ጋር ጠላት ነትያወጀዉ አላስኬድ አላሳልፍ ስለአለ

ነዉ፡፡* ዐማራዎች ሲመነጠሩ ሌላዉ ኢትዮጵያዊ የሚቆጣ ኢትዮጵያን የማፈራረሱ ዓላማዉ ሲፈጸም ወለል ብሎ ስለታያቸዉ እንጂ ዐማራ ስለሆኑ እና ለ ዐማራ አድልተዉ እንዳልሆነ ዐማራዉ ይረዳል ፡፡ማለቱ

* ወርቅ ከሆነ ዘር መወለዴ በጣም ያኮራኛል ፣*ዓማራ እና ኢምፐሪያሊዝም የትግሬ ቀንደኛ ጠላቶች ናቸዉ ፣ *ዐማራ ጠላትህ ስለሆነ ተጠንቅቀህ ጠብቅ፡፡ ዶሮ እግሯን አስሮ ቢለቋት የፈቷት ይመስላታል ብሎ መተረቱ፣*በ1997 ምርጫ አሸናፊ ለቅንጅት ለምን ሰልጣን አታስረክቡም ሲባል እኛ ለአማራ ሥልጣን አንሰጥም ፣*በ1997 ዓ.ም ከሁለት መቶ በላይ ሰዎች ሲገደሉ ለምን ለማስፈራራት ወታደሮች ወደ ሰማይ አይተኩሱም ሲባል ከአሞራ ጋር አልተጣላንም በማለት ማፌዙ፣* ቅንጅት እኮ የዐማራ ድርጅት አይደለም ትግሬዎችም አሉበት ሲባል ናዚ ዉስጥም አይሁዶች ነበሩበት

*አንተም በሚል እርስ ጋዜጠኛዉ ብዙ ኢትዮጵያዊ አሰብ የኢትዮጵያ አካል ናት ይላሉ ሲለዉ እነዚህ ህልመኞች ዐማራ፤አሰብ የኤርትራ እንጂ የኢትዮጵያ አይደለችም፡፡ እንዲያዉም እስከ አሁን የተጠቀመችበትን ሂሳብ ወደኋላ ተመልሰን እንጠይቃለን ነዉ የአሉት ፣ *የነጻትምህርት እድል 100ፐርሰንት ለትግሬ ይሰጣል ሲባል ዐማራዉ ቀድሞ ስለተማረ ነዉ ለትምክተኛ ዐማራ ስልጣን አንሰጥም፣* የነፍጠኛዉ ተረት እና ታሪክ የኢትዮጵያ ህዝቦች በሙሉ ታሪክ አድርገዉ ነዉ የሚተርኩት የተዋረደዉን ታሪካችን በአዲስ መልክ እንመሰርታለን የኔ ምኞት ዐማራ ከመንገድ ላይ ቁጭብሎ ሲለምን ማየት ነዉ

*ለኢትጵያ ፓርላማ ስለሱዳን ድንበር ሲናገር የኔን ለኔ የናንተን እንካፈል የሚለዉን የተስፋፊነት አቋም ችሎ ባደረ የሱዳን መንግስት እንደ እንዝላል ሊቆጠር አይገባም እንደ አስተዋይ እንጂ በ1996 ዓ.ም የኢትዮጵያ ጦር ሂዶ የያዘዉን መሬት ነዉ የሰጠነዉ የተፈናቀለ ዐማራ የለም በብሄራዊ ጥያቄ ዙሪያ አቋምን ተጠቅመን ከሌሎች ጋር በመተባበር ዐማራን ለማጥፋት አቅደን ተነሳን በማለት በየስብሰባዉ፣በየሄደበት ስለዐማራ ህዝብ ከኢትዮጵያ ተነጥሎ እንዲጠፋ ለማድረግ ቁሞም ተቀምጦም የሚያነበንበት ሥር የሰደደ ምክንያት ምን ይሆን

፫-- ሳሞራ ያኑስ -- አባቶቻችሁን ገድለን ቀብረናቸዋል፡፡እናንተንም ገድለን እንቀብራችኋለን በአንበሳ ባንክ ምስረታ ጉባኤ ላይ ተገኝቶ ገድለን የቀበርነዉን ዐማራ አታንሱብኝ .ለራሳቸዉ ነጻነት የሚዋጋዉን ወታደር ከጦርነት መልስ ስንት ዐማራ ገደልክ ማለቱ

፬---አቶ ጌታቸዉ እረዳ በነጻነት ኢትዮጵያ ቃለመጠይቅ ትግሬ በአማራ የሚጠራ ስድብ ነዉ፰-፬--፬-፬ --ታምራት ላይኔ-- በአርባጉጉ አዉራጃ ህዝቡን ሰብስቦ እናንተ ሽርጣም እየተባላችሁ ስትጨፈጨፉ ስትገዙ የነበራችሁ ዛሬ ጊዜዉ የናንተ ነዉ ዝምብላችሁ ታዩታላችሁ በማለት

የዐማራዉን ህዝብ ማስጨፍጨፉ፣ በ1984 ዓ.ም በአርባጉጉ አዉራጃ በገፍ ሲጨፈጨፉ በኩማ ደመቅሳ የተመራ ደራ የተባለ ኃይል አቶ አቻሜላህ አሰፍን በቁማቸዉ ቆዳቸዉ ሲገፈፍ እርጉዟ ሆዷ ተቀዶ ሽሏ ከፊቷ ሲወድቅ ለታምራት አቤቱታ ሲያቀርቡለት ሀረር ብሎ፣ አሩሲ ብሎ፣ ባሌ ብሎ ዐማራ አላዉቅም ብሎ መመለሱ። የዳኝነት መልሰ መነፈጉ፡፡ የመሳሰሉትን አባባሎች ለአብነት ማየቱ በአማራ ሕዝብ ላይ ያላቸውን የጥላቻ ጥግ ገምግሞ ራስን ከጠላት መንጋጋ መከላከል አልሞት ባይ ተጋዳይነት ነው።

ለዚህ ስር የሰደደ የአማራ ሕዝብ ጥላቻቸው ምክንያታቸው ምን ይሆን? በሚል ለማጣራት በተደረገዉ ጥረት እስከ አሁን ሁለት ምክንያቶች ተገኝተዋል፡፡

1.ምእራባዊያን ሀገሮች የስዊዝ ካናሉን እና አባይን ከምንጩ ለመቆጣጠር ያመቻቸዉ ዘንድ አፍሪካን ወሮ ለመያዝ በ1884 ዓ.ም የአሳለፉትን ዉሳኔ ተግባራዊ ለማድረግ በኢትዮጵያዊያን በአድዋ ጦርነት የማያዳግም ድል ተመተዋል፡፡ ባንዳዎችም አብረዉ ተመተዋል። እነ መለስ እና ቡድኑ የባንዳ ልጆች እናየልጅ ልጆች ናቸው። ለዚህም ተዋጊዉ ነፍጠኛዉ ዐማራ ሕዝብ ነዉ ብለዉ ያምናሉ። በተጨማሪም በምድኛ ዙሪያም በናቶቻቸዉ የዐማራዉን ሕዝብ በሙሉ በጠላትነት ተግተዉ የአደጉ መሆናቸዉ ነዉ፡፡

ለዚህም ማስረጃ የሚሆነ አስራት አብርሃ «ከአገር በስተጅርባ። የተባለዉን መጽሀፍ የጻፈዉ አስራት አብርሃ ስለ አማራ አዉሬነት በአጠቃላይ ስለዐማራ በማጥላላት እንደ አሰደገችዉ እና በኋላ ሲያድግ ሃሰት መሆኑን መረዳቱ ነዉ፡፡በዚህ ምክንያት የአባቶቻቸዉን አለቆች ደም ለመመለስ የምእራባዊያንን ኢትዮጵያን የማፍረስ ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያደርጉት መፍጨርጨር ነዉ፡፡

2 . በፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት እና አቶ አሸናፊ የሚኒልክ ልጅ የተደረገ ቃለ ምልልስ የተገኘ የዐማራዉ የማንነት ታሪክ ነዉ፡፡ ታሪኩም እንዲህ ይነበባል፡፡ የጥንት ዐማራዎች የዮቶር ልጆች ናቸዉ፡፡ዮቶር የዛሬ አምስት ሺህ ዓመት በጌምድር የሚኖር በግ አርቢ ነበር፡፡ ለንግድ እና ለተለያዩ ተግባራት ወደ ባህሩ በመምጣት መንግስታቸዉን መሰረቱ፡፡ይህም የዳማት(ዘዐማራ) መንግስት ነዉ፡፡

የመጀመሪያ ንጉሳቸዉ አክናሁስ ይባላል የግዛታቸዉ ድንበር እጅግ ሰፊ እየሆነ ሲመጣ የንጉሱ መጠሪያ የአገር ሹም(አግሹም፣አክሹም) በጊዜ ሂደት አኩሱም ይባል ነበር ፡፡ ንጉሱ በዚህ ስም መጠራት የጀመሩት ክርስቶስ ሊወለድ አምስት መቶ ዓመት ሲቀረዉ ነዉ፡፡ የግዛት ስፋቱ ከስሜን ቀይባህር እስከ በናዲር(የአሁኑ ሞቃድሾ) የእሱ ግዛት እንደነበር የታወቀ ነዉ፡፡

የጥንት የዐማራ ነገስታት አኩሱም ላይ ሁነዉ ጠንካራ ንግድ ከፋር ኢስት እና ከጥንት ቻይናዎች ጋርመሰረቱ ፡፡በዚህ ምክንያት ከፍተኛ ሀብት ተፈጠረ፡፡በአካባቢዉ ለሚሰሩ ግንበኞች፣ለቀን ሰራተኞች እና ለቤት ዉስጥ ታዛዥ እና አገልጋይ ለመሆን ከተለያዩ ሀገራት

ሰዎች ይመጡ ነበር፡፡እነዚህ ከተለያየ ቦታ መጥተዉ አኩሱም የተለያየ የቀንሥራ የሚሰሩትን በሙሉ የሀገሬዉ ሰዉ የሚጠራቸዉ ትግሬ እያለ ነበር፡፡ያንጊዜ ትግሬ የብሄር ስም ሳይሆን የሥራ ስምነዉ፡፡ ያን ጊዜ ትግሬ ማለት አገልጋይ ማለት ነበር፡፡ ዋና ምንጫቸዉም ከሰሜን የመን ነበር፡፡ይህ ታሪክ በሳይንሳዊ መንገድ ተጠንቶ የተደረሰበት ነዉ፡፡

ለምሳሌ* አብዛኛዉ ትግሬዎች ከግንባታ ሥራ ጋር መዋደዳቸዉ፣*አኩሱም ላይ ባሉ ሀዉልቶች እና ቤተመንግሥታት ትግሬነትን የሚያሳይ ምንም ዓይነት የጽሁፍም ሆነ የቅርጻቅርጽ መረጃ አለመኖሩ፣

2 .ያንጊዜ ምግብ በሞሰበወርቅ ለአሰሪዎቻቸዉ አቅርበዉ ክዳኑን ይዘዉ ወደ ማጀት ሲመለሱ በአሁኑ ጭፈራቸዉ ላይ መንጸባረቁ ፤ይኸዉም የሞሰበወርቅ ክዳን ይዞ በአንድ እግር እየዘለሉ መጨፈር፤

3 .ከነሱ በፊት በመጡትአስራ ሁለት ሺህ ፈላሻዎች በመገፋታቸዉ አኩሱም ላይ ብቻ መወሰናቸዉ፤

2 . ከሰሜን የመን ይዘዉት የመጡት ሳባዊ ቋንቋ በግእዝ ተጽእኖ ምክንያት የአገልጋይዎች ቋንቋ ወይም አሁን ትግሬኛ መፈጠሩ፤

5 . ትግሬ የሚለዉ ቃል በራሱ ትርጉም አገልጋይ ማለት መሆኑ፤

6 የትግሬ ወደ አኩሱም መምጣት ዛሬ በዲቪ ወደ አሜሪካ በመሄዳቸዉ እንደሚደሰቱት ነበር፤

.ዐማሮች ያን ሰፊ ግዛት በጥሩ ሁኔታ ለማስተዳደር ሲሉ አንዱን አኩሱም አንዱን ደግሞ ኤረር ላይ ነገሱ፡፡ይህም በአራትመቶ ዓ.ም ነበር፡ ኤረር ማለት የአሁኑ ሸዋ አዲስ አበባ ዙሪያ ማለት ነዉ፡፡ ክርስትና እዉቅና ያለዉ ሃይማኖት በመሆኑ የተበሳጩት ፈላሻዎች ጥሩ ቀን ይጠባበቁ ነበር፡፡ይህንም በዘጠኝ መቶ ዓ.ም አገኙት በበቂ ሁኔታ ያልተዘጋጀዉን የአኩሱሙን መንግስት አሸነፉት፡፡የሸዋን መንግስት ለመዉጋት ዘምተዉ ተሸነፉ መራቤቴ ላይ በጦርነት አለቁ፡፡ ከአርባዓመት ጦርነት በኋላ ፈላሾች ዉድመት ብቻ አተረፉ፡፡

አኩሱም ተሰደዉ የመጡት የአኩሱም ዐማራ ነገሥታትም ከዚሁ ሸዋ ሁነዉ ማስተዳደር ቀጠሉ፡፡ግማሾቹም ላስታ ሂደዉ አስተዳዳሪ ሆኑ፡፡የታሪኩን ሁኔታ ለማስተማር የዐማራ ምሁራን ዝምታን መረጡ፡፡ዝምታ ደግሞ ሰላም ያደፈርሳል፡፡ይህ እዉነተኛ ታሪክ ነዉ፡፡ በሃሰት የሚፈጠር ሰላም ዘላቂ አይደለም ሲል በቃለ ምልልሱ አስረድቷል፡፡

በነዚህ ሁለት ምክንያቶች መለስና ቡድኑ የበታችነት ስሜትን በአዕምሮአቸዉ በመሳል እና በሌላዉም ላይ የነሱ ዓይነት አስተሳሰብ እንዳለ በማሰብ ይህን እዉነታ እንገለብጣለን በሚል መነሻቸዉን ዉሸት እና እምነት አድርገዉ በምእራባዊያን አበረታችነት ዐማራን ለማጥፋት ዓልመዉ እና አቅደዉ ለትግል የተነሱ ናቸዉ፡፡

የሰዉ ልጅ እዉነትን መደበቅ ከቻለ መደበቂያዉ ዉሸት ነዉ፤እንጅ ሌላ ሊሆን አይችልም፡፡ ሰዉ እየዋሸ ለመሆኑ ምልክቱ የተጠየቀዉን ትቶ ሌላዉን ማዉራት፣ የተቀመጡበትን ወንበር ማሽከርከር፣እጅ ማወራጨት፣ በብዛት ለማዉራት መጣር፣ማደናገሪያ ሃሳብ ማቅረብ ይህ ሁሉ አልሳካ ሲል ማጥቂያ መንገዱ ቁጡነት ነዉ፡፡ይህ ደግሞ የሚመነጨዉ ከተሸናፊነት ፣ ከበታችነት ስሜት በመነሳት እራስን ከፍ ከፍ አድርጎ ለማቅረብ በማለም ነዉ፡፡ ለዚህም ነዉ መለስ እና ቡድኖቹ የበታችነት ስሜታቸዉ እየአሰጨነቃቸዉ ይህን ለመቆጣጠር ሲሉ በቁጣእና በስድብ በመንግስት መ/ቤት የሚሰራ ሁሉ ሳይልኩት ወዴት ሳይጠሩት አቤት እያል የርዕደት ዘመኑን ያሳለፈዉ እነሱም እኛ ወርቆቹ እያሉ ያላዝኑ የነበሩት፡፡

እዉነት ከተፈጥሮ ጋር የማትገጥም እና አድካሚ ተቃራኒ ነገር በመሆኗ ፊቷ አንድ ብቻ ነዉ፡፡ ጀርባዋ ግን ብዙ ብዙ ዉሸት ይይዛል፡፡መለስ እና ቡድኑ የዉሸት ፈጠራ ታሪካቸዉን ምክንያቶችን ጨማምረዉ እና ቀባብተዉ የሚሰጧቸዉ የአዋቂነት ትንታኔዎች ብለዉ የሚያስቧቸዉ ሁሉ ዉሸት ናቸዉ፡፡ የዐማራ ህዝብ ሊረዳዉ እና ሊከተለዉ የሚገባ እዉነት በብዙ ዉሸት ተደብቃ ያለች እና ዉሸትን ገላልጦ እዉነትን አዉጥቶ የኑሮአችን አካል ለማድረግ፤

1ኛ አድካሚ እናጊዜ ፈጅ መሆኑን ማወቅ፡፡

2 መለስ እና ቡድኑ ለዉሸት ማስፈጸሚያ አድርገዉ ለልጆቻቸዉ አስተምረዉ እና በጽሁፍ ሰንደዉ በዉርስነት ያስተላለፉት በኢኮኖሚ የበላይነት እና በጦርነት አጥቂ ሁኖ መዉጣትን ነዉ፡፡ዐማራዉ ይህን አዉቆ ለአንድ አፍታም ሳይዘነጋ በሚመጡበት አቅጣጫ ሁሉ አጸፋ መልስ ለመስጠት ዝግጁ ሁኖ መገኘት ነዉ፡፡ ሕዝብን አንቅቶ እና አደራጅቶ ዐማራን ብሎም ኢትዮጵያን ለማጥፋት አዝለዋቸዉ ከሚመጡት ጋር ዳግሚያ አድዋን ለማሳየት ከአገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ጋር መሰለፍ ነዉ፡፡

ዐማራነት ሃይማኖት ለሚመስላቸዉ እና ህሊናቸዉን ለገንዘብ እና ለስልጣን ለሚሸጡ ምሁራን አማራነት ነገዳዊ(ደማዊ)የጥንት ማንነት መሆን እያወቁም ሆነ ሳያዉቁ አማራ የለም ብለዉ ለሚክዱ ታሪካዊ ማስረጃዉ እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

በመካከለኛ ዘመን የመን በሙስሊም ዐምሃራ ሥርዎ መንግስት ስትስተዳደር ከአኩሱም መንግስት ወደየመን ተሸግረዉ የመን ይገዙ የነበሩ ሙስሊሞች ዐምሃራዎች ነበሩ፡፡ የነዚህ ሙስሊም ዐምሃሮች ስርዎ መንግስት ነጃሄድ ሥርዎ መንግስት በመባል ይታወቅ ነበር፡፡ይህ የመንን የገዛዉ የሙስሊም ዐምሃራ ሥርዎ መንግሥት መቶ ዓመት አስተዳድሯል፡፡ የሥርዎ መንግሥቱ ቆርቋሪ ሙኢያድ ነጃህ ይባል ነበር፡፡ እሱን እየተኩ የነገሱ ሙስሊሞች አሊዳኢ ሱላይሂድ፣ሰኢድ አህወልነጃህ፣ጀያሽ ነጃህ፣ፈቲህ ጀያሽ፣መንሱር ፈቲህ፣መንሱር ፈቲህ ዳግማዊ፣ ሙሃመድ መንሱር፣ፈቲህ ሳልሳዊ ናቸዉ፡፡ከነዚህ ሁሉ ታዋቂ የነበረዉ ሙህመድ መንሱር ዐምሃራ አልፈቲህ ይባል ነበር፡፡የአረቡ ጸሀፊ ኢብን ኸልዱን ስለሱ እንዲህ

ሲል ጽፏል፡፡ ሙሀመድ ሱሩር ዐምሃራ አልፈቲህ ከሀበሻ ዘር ከዐማራ ነገድ የሚወለድ ንጉስ ነበር ይህ ሙስሊም ዐምሃራ ንጉስ የመንን በማስተዳደርበት ዘመን እጅግ ታላላቅ ሥራዎችን የሰራ መሆኑን ጽፏል፡፡ከመካከለኛዉ ዘመን በፊት የመን የኢትዮጵያ የአኩሱም መንግሥት አካል እንደነበረች ይታወቃል፡፡ አኩሱም ከፈረሰ በኋላ የዐማራ ዘር የመንን ለመቶ ዓመት እንደ አስተዳደረ የታሪክ ሰነዶች ይናገራሉ፡፡ ዐማራነት ሃይማኖታዊ ግድብ የሌለዉ ከመሰረቱ የደም ማንነት ነዉ፡፡ ምንጭ

Ibn khaldumu YAman its early medieval history irans H.C kay(London 1892 ) ገጽ 117

ከሙላት በላይ